## <u>መዘከር</u>

<u>ከርሞ ጥጃ</u>

ጊዜው ሁሉ አጠቃሎ ለተግባሩ አመችቶት
ሜዳው መቦረቂያው ሁሉ አልበቃ ብሎ አስቸግሮት፣
የጠገበ ጥጃ ሆዱ ሞልቶ ምን ሊያቅተው ምን ተስኖት
ባለሞያው ሁሉ ጠፍቶ ማን ሊገታው ማንስ ነክቶት።

ይጨፍራል ከግራ ቀኝ ወዲያ ወዲህ ይራወጣል
ከላይ ታች ያሻውን ሁሉ እያነሳ ያስቀምጣል፣
ሁሉም ተንከባክበው እየተለማመጡ ሲያቀርቡለት
የፈለገውን ሲበላ እየመጠመጠ ሲጠባ የእናቱን ጡት።

ቀኑ ይነጋል ይመሻል ሳምንትም ይመጣል ይሄዳል
ወሩ ከምኔው ይደርሳል ዓመትም ሳያስቡት ወዲያው ያልፋል፣
እንዲህ እያለ ጊዜው እየፈጠነ በጣም ሲሮጥ
ጥጃም ጥጋቡ ይበርድና ሃሳቡ ሁሉ ሲናወጥ
መቦረቂያው ጊዜ ተንሸራቶ ሲያልቅና ወረቱ ሁሉ ሲሟጠጥ፣
ልጅ ወተት ሲያልቅበት አብቅታ ስትጠግግ ላሚቱ
የሚቀመስ ሲታጣ እንደልብ የሚሰጠው መድኃኒቱ።

ጊዜው ሲሄድ ሲሄድ ሲሄድ ብቻ ሲቆጠር የባከነ
ጥጃም ላያድግ ላይዳብር ላይለወጥ ላያብብ ላያፈራ ያልሰከነ፣
ውሎም አድሮ ሰንብቶ ወራት ዓመታትም ተቆጥረው
የዕድሜ ብዛት ብቻ ፈጽሞ ሕገ ወጥነቱን ላይገታው
መላ ቅጡም አልለየለት ማደናበር ማደናገር የመቧረቅ መባቻው።

የመዝለያ ዕድሜው የመማሪያ ማላገጫው
መጠኑ መጠር ነበረበት የመቀለጃ መጫወቻው፣
ሲታሰብ ሲጻፍ ሲተረክ ሲነገር በጊዜው ፍጻሜ ተስተዋለ
የልጅነት የዋህነት ወንጀል መደምደሚያ ወቅቱ ገና ነው ተባለ።

ዓለማየሁ አስፋው/ ቶሮንቶ